## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን



### ሥነ-ፍጥረት






kids23



# ይቀጥላል--


- እሑድ የሚለው አሐደ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን አንድ አደረገ ወይም የመጀመሪያ ማለት ነው።" -በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ።" ዘፍ፤ 1፣1
- አራቱ ባሕርያት የእነዚህ ፍጥረታት እግዚአብሔር አምላክ በባሕርይው አራት ነገሮች እንዳሉት ለማጠየቅ ። እነዚህም ባዕልነት /ባለጸጋነት/፣ ርኅሩኅነት /ቸርነት/ ፣ ከሀሊነት /ሁሉን ቻይነት/፣ ፈታሒነት /ፈራጅነት/ ናቸው።
- ሰማያት የተፈጠሩት ከእሳት ሲሆን ከእሳት ብርሃኑን ወስዶ ሙቀቱን ትቶ ፈጥሯቸዋል። ሰባቱ ሰማያት የሚባሉትም፡-
- 1ኛ. መንበረ መንግስት፡- በዚህ ቦታ እግዚአብሔር እንደወደደ ለቅዱሳኑ የሚታይበት ነው። ለነቢዩ ሕዝቅኤል ሕዝ፤ 1፣26 ፤ ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ራዕይ፤ 4፣2
- 2ኛ. ጽርሐ አርአም፡- ሥላሴ በመንበራቸው ላይ ሆነው የሚሰለሱት፣ የሚቀደሱት በዚህ ሰማይ ነው። ሰባት የእሳት መጋረጃ ተጋርዶበታል ፣ሰባት የእሳት ቅጥር ተቀጥሮበታል። - ሰባቱ የእሳት መጋረጃ በየት ተዘጋጀ? በየትስ ተተከለ?"
- 3ኛ. ሰማየ ውዱድ፡- ይህ ሰማይ የሥላሴን ዙፋን የተሸከሙት አራቱ እንስሳት /ገጸ ሰብዕ ወይም የሰው መልክ ያለው፣ ገጸ አንበሳ፣ ገጸ ንስር ወይም ወፍ፣ ገጸ ላህም ወይም የላም መልክ ያላቸው/ የሚገኙበት ሰማይ ነው።
- 4ኛ. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፡- ሳጥናኤል የተፈጠረው በዚህ ቦታ ነው። መንግስተ ሰማያት የምትባለው ይህቺው ሰማይ ናት። የእመቤታችን ምሳሌ የሆነችው ታቦት ዘዶር የምትገኘው በዚህ ሰማይ ነው።
- 5ኛ. ሰማየ ኢዮር፡- 6ኛ. ሰማየ ራማ፡- 7ኛ. ሰማየ ኤረር፡-
- ከዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት ጀምሮ ለፍጥረት ሰባተኛ የሆኑት መላዕክት ተፈጥረዋል።
- የዕለተ እሑድ የመጨረሻውና ስምንተኛው ፍጥረት ብርሃን ነው።

# 7ቱ ሰማያት






፱ኙ ነገደ
መላዕክት
ቅዱስ ሚካኤል
ቅዱስ ገብርኤል
ቅዱስ ሩፋኤል
ቅዱስ ዑራኤል
ቅዱስ ራጉኤል
ቅዱስ ፋኑኤል
ቅዱስ ሳቁኤል
ቅዱስ ሱራፌ
ቅዱስ ኪሩብ
ኃይላት
አርባብ
መናብርት
ሥልጣናት
መላዕክት
ሊቃናት
ሱራፌል
ኪሩቤል
7ቱ ሊቃነ መላዕክት
አርባዕቱ እንስሳ
መንበሩን ተሸክመው
የሚያመሰግኑት ናቸው



ኢዮር
1ኛ ከተማ
10
ኢጋዕዝት
ሳጥናኤል
2ኛ ከተማ
10
ኪሩቤል
ኪሩብ
3ኛ ከተማ
10
ሱራፌል
ሱራፊ
4ኛ ከተማ
10
ኃይላት
ቅዱስ
ሚካኤል

# ይቀጥላል---

- 1ኛ ኢዮር ካሉት መላእክት ከነገደ ኪሩቤል ገጸ- ሰብዕና ገጸ - አንበሳን፣ ከነገደ ሱራፌል ገጸ-ላሕምና ገጸ-ንስር መርጦ በሰማየ ውዱድ አኖራቸው።
- ነገደ ሱራፌል ባለስድስት ክንፍ ሲሆኑ ነገደ ኪሩቤል ባለ ብዙ ዓይኖች ናቸው። ራዕ፤ 4፣6-8 ኢሳ፤ 6፣3
- 2ኛ. በሰማየ ራማ ካሉት መላዕክት ሃያ አራት ሊቃናትን መርጦ በመንበረ መንግስት ዙሪያ ክንፍ ለክንፍ አያይዞ አቆማቸው።
- የብርሃን ዘውድ ደፍተው፣ የብርሃን መስቀል ይዘው፣ የብርሃን ማዕጠንተ ወርቅ ጨብጠው የሚያመሰግኑ እና መንበሩን የሚያጥኑ አድርጓቸዋል። ራዕ፤ 4፣4 እነዚህ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ የሚባሉት ሲሆን
- 3ኛ. በኤረር ካሉት መላዕክት ሃያ አራት ሺህ መርጦ ለሰማይ አስራ ሁለት ሺህ መስኮት አበጅቶ
- በእያንዳንዱ መስኮት ሁለት ሁለት መላዕክትን አስፍሯቸዋል። እነዚህ መላእክት ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በመብረር ዓለምን በሙሉ ይቆጣጠራሉ።



ይቀጥላል--------


ኤረር
ኛ ከተማ
10
2ኛ ከተማ
10
3ኛ ከተማ
10
መኳንንት
ቅዱስ
ሰዳኪያል
ሊቃናት
ቅዱስ
ሰላትያል
መላእክት
ቅዱስ
አናንያል

# የሰኞ ፍጥረታት

- ሰኑይ ማለት ሁለተኛ ወይም ሁለት አደረገ ማለት ነው።
- በዚህ ቀን የተፈጠረው አንድ ፍጥረት ሲሆን ይኸውም ጠፈር ነው።
- በዕለተ እሑድ የተፈጠረው ውሃ ከእሑድ እስከ ሰኞ ድረስ ከምድር እስከ ብሩህ ሰማይ ኤረር ድረስ ሞልቶ ነበርና "እግዚአብሔር አምላክ ሲያዘው ለሶስት ተከፍሏል። አንዱን እጅ "- በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን" ዘፍ፤ 1፥9 ብሎ ውሃን እንደ ብረት አጠንክሮና አጽንቶ ጠፈርን ፈጥሮታል።
- አንዱን እጅ የውሃው ባሕርይ ሳይለወጥ ከጠፈር በላይ ሰቅሎ አስፍሮታል። ይኽም ሐኖስ ሲለው፤
- አንዱን እጅ ደግሞ በምድር አስቀርቶታል። በምድር የቀረውን ውሃ እንዲሁ ለሶስት የተከፈለ ሲሆን አንዱ እጅ ከምድር በታች የሰፈረው ባሕር ነው። ምድር የጸናቸው በዚህ ውሃ ነው።
- ቅዱስ ዳዊት "- ምድርን በውሃ ላይ ያጸናህ" መዝ፤ 135፥6 እንዳለው።
- ምድርን እንደመቀነት የከበበት እውቅያኖስ
- በዚህ ቀን በመጀመሪያ ሰዓተ ሌሊት ጠፈር የተፈጠረ ሲሆን ጠፈር ከተፈጠረ በኋላ የቀረውን ሃያ ሶስቱን ሰዓት ምን ሰርቶበታል ቢሉ መላእክትን ቦታ ቦታ ሰጥቶ ለአገልግሎት አሰማርቷቸዋል።

# ይቀጥላል--

- በዕለተ ሰኑይ ፍጥረት ምስጢረ ሥጋዌ ተገልጿል፡፡ ይህም ከምድር እስከ ብሩህ ሰማይ ኤረር ድረስ የሞላው ውሃ ከሶስት ከፍሎ ሁለት እጁን ማለትም ጠፈርንና ሐኖስን ከላይ ማስፈሩ፤ ሥጋ ለብሰው አልታዩምና የአብና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፡፡
- አንዱ እጅ ወደ መሬት መውረዱ ከሶስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ በተለየ አካሉ ከሰማየ ሰማያት ወደ ምድር ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ከብሮ የመወለዱ ምሳሌ ነው፡፡

# እሑድ እና ሰኞ

1. ጨለማ
2. መሬት
3. ውሃ
4. እሳት
5. ነፋስ (አየር)
6. ሰባቱ ሰማያት
7. መላእክት
8. ብርሃን

- ጠቢባን ስላሴ ከዕለታት መርጠው ዓለምን የፈጠሩት በዕለተ እሑድ እና ሰኞ ሲሆን ‘ዕለተ ጠቢባን’ ይባላሉ። ዓለማት ተፈጥረው ያለቁት በእነዚህ ሁለት ቀናት ነው።

# የማክሰኞ ስነፍጥረት

- ሠሉስ ማለት ሶስት ማለት ነው ይህ ቀን ፍጥረታት መፈጠር ከተጀመሩ ሶስተኛ ቀን ሆኗልና ሰሉስ /ሶስተኛ/ተብሏል
- በተለምዶ ማክሰኞ ብንልም ትክክለኛው ግን ማግሰኞ ሲሆን የሰኞ ማግስት ማለት ነው፡፡
- ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርን ቡቃያን በምድር ላይ እንደወገኑ እንደወገኑ ዘር ያለበትን፣ ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል ብሎ እግዚአብሔር አዘዘ እንዲህም ሆነ" ዘፍ፤ 1፣12
- በዚህ ትዕዛዝ ሶስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል፡፡ እነሱም፡-
  - · በምሳር /በመጥረቢያ/ የሚቆረጡ ዕጽዋትን፣
  - በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕትን፣
  - በእጅ /በጣት/ የሚለቀሙ አታክልትን

# ከዕለተ ሠሉስ ፍጥረታት ምን እንማራለን?

- በስራቸው የሚያፈሩ፣ በጎናቸው የሚያፈሩ፣ በስራቸው የሚያፈሩ አሉ።
- በስራቸው የሚያፈሩ: በሚስቶቻቸው / በባሎች/ በልጆቻቸው የሚጠቀሙ፤ በጌታ ትምህርት አምነው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ ነው።
- በጎናቸው የሚያፈሩ፡- በሰራተኞቻቸው፣በጎረቤቶቻቸው የሚያምኑ፣ በሐዋርያት ስብከት ያመኑ፣ በጥምቀት የዳኑ ሰዎች ናቸው።
- በጫፋቸው የሚያፈሩት ደግሞ በራሳቸው ጥረው ግረው ራሳቸውን የሚረዱ፣ የሚያድኑ፣ እንዲሁም በሌሎች መምህራን ትምህርት ያመኑ የክርስቶስን ሞቱን፣ ትንሳኤውን አምነው በመስቀሉ የዳኑ ሰዎች ምሳሌ ነው።
- ሚስጥሩ ደግሞ በስራቸው የሚያፈሩ ባለ ሰላሳ፣ በጎናቸው የሚያፈሩ ባለስልሳ፣ በጫፋቸው የሚያፈሩት ባለመቶ ፍሬ የሚያፈሩ ሰዎች ምሳሌ ናቸው። ማቴ፤ 13፣1

# ይቀጥላል----

- ፍሬያቸውን በስራቸው፣ በጎናቸው በጫፋቸው የሚይዙ / የሚያፍኑ/ አሉ። በስራቸውና በጎናቸው በመሸፈን ከወፍ ከጠላት የሚከላከሉ፤ መልካም ትሩፋትን ሰርተው ነገር ግን እኛ አላደረግንም የሚሉ ቅዱሳን ምሳሌ ናቸው።
- ፍሬያቸውን በጫፋቸው በመያዝ ወፍ የሚበላባቸው፣ ጠላት የሚያጠፋባቸው ደግሞ የሰሩትን በጎ ስራና ትሩፋት እንዲያዩላቸው በመፈለግ፤ ይወቁልን፣ ይስሙልን የሚሉ ሰዎች ምሳሌ ናቸው። ማቴ፤ 6፣1
- ከእነዚህ ፍጥረታት መካከል በአንድ መሬት ላይ በቅለው ግማሹ ጣፋጭ ፍሬ ያላቸው፣ ግማሹ መራራ ፍሬ ያላቸው አሉ። ይኸውም በአንዲት ምድር ላይ የተፈጠሩ የሰው ልጆች ግማሹ መልካም ስራ በመስራት ፈጣሪያቸውን የሚያስደስቱ ፣ ሌላው ደግሞ በመጥፎ ስራቸው በመኖር እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ ሰዎች ምሳሌ ነው።

# ይቀጥላል----

- ዕጽዋት፣ አዝርዕት፣ አታክልት፡- አበባ የሌላቸው ፍሬ ያላቸው አሉ፣ አበባ ያላቸው ፍሬ የሌላቸው አሉ፣ አበባም ፍሬ የሌላቸው፣ አበባና ፍሬ ያላቸው አሉ።
- አበባ የሌላቸው ፍሬ ያላቸው፡- ሃይማኖት ሳይኖራቸው ምግባር ያላቸው ምሳሌ ናቸው
- አበባ ያላቸው ፍሬ የሌላቸው፡- ሃይማኖት ያላቸው ምግባር የሌላቸው ምሳሌ፤
- አበባም ፍሬ የሌላቸው፡- ምግባርም ሃይማኖትም የሌላቸው ምሳሌ፤
- አበባና ፍሬ ያላቸው ደግሞ ምግባርም ሃይማኖትም አስተባብረው የያዙ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።

# ይቀጥላል-----

- ከማክሰኞ ፍጥረታት መካከል በሰኔ ተዘርተው የክረምቱን ዝናብ ተቋቁመው ለፍሬ የሚደርሱ አሉ፤ ይኸውም ብዙ መከራና ስቃይ ተቋቁመው ለክብር የሚበቁ ቅዱሳን ምሳሌ ናቸው። እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያሉ።
- - እኛስ በብዙ መከራ የእግዚአብሐርን መንግስት እንወርሳለን" ሐዋ፤ 14፣21
- በሌላ በኩል በክረምት መውጫ ተዘርተው በጥቂት ዝናብ በቅለው ለፍሬ የሚበቁ አሉ። ይኸውም በጥቂት ምግባርና ትሩፋት የሚጠቀሙ፣ እንዲሁም አንድ ቀን መከራን በመቀበል የእግዚአብሔርን መንግስት የሚወርሱ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።

# ይቀጥላል----

- በተጨማሪም ክረምት ለምልመው በጋ የሚደርቁ፣ ክረምት ደርቀው በበጋ የሚለመልሙ ዕጽዋት፣ አታክልት፣ አዝርዕት አሉ።
- በክረምት ለምልመው በበጋ የሚደርቁ፤ በዚህ ዓለም ሳሉ በልተው፣ ጠጥተው፣ ለብሰው፣ ደምቀው አምሮባቸው የሚኖሩ በሚመጣው ዓለም ተስፋ ነፍስ የሌላቸው ምሳሌ ናቸው። እንደነማን? ያሉ ቢሉ እንደ ነዌ፣
- በክረምት ደርቀው በበጋ የሚለመልሙት፤ በዚህ ዓለም ተርበው፣ ተጠምተው፣ታርዘው፣ አከው የሚኖሩ በወዲያኛው ዓለም ግን ተስፋ ነፍስ ያላቸው ናቸው። እንደነማን ? ቢሉ እንደ አልዓዛር ያሉ ናቸው።
- ደግሞም ክረምትም በጋም የማያፈሩ፣ የማይለመልሙ አሉ፤ እነዚህ በዚህ ዓለም ሳሉ ተቸግረው፣ አዝነው፣ ተክዘው፣ ኀስቁለው አከው የሚኖሩ
- ነገር ግን የደረሰባቸውን በኢኮቴት የማይቀበሉ ነገር ሀጢአት በመስራት በመስረቅ፣ በመቀማት ኖረው በወዲያኛውም ዓለም ሳይጠቀሙ የዲያብሎስ ባሪያ ሆነው የሚቀሩ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።
- “ድሃውን ስለድህነቱ አይምረውም እርሱን ደስ ካላሰኘው” እንዳለ ቅዳሴ አትናቴዎስ፤
- በሌላ በኩል በክረምትም በበጋም አፍርተው፣ ለምልመው የሚኖሩ አሉ። እነዚህም በዚህ ዓለም በተድላ በደስታ ኑረው በሃብታቸው ተግባረ ጽድቅ ሰርተውበት በወዲያኛው ዓለም የሚጠቀሙ ሰዎች ምሳሌ ነው። እነዚህ እንደ አብርሃም፣ እንደ ይስሐቅ፣ እንደ ያዕቆብ ያሉ ናቸው።

# የረቡዕ ስነ ፍጥረት

- ረቡዕ ረብዓ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን አራት አደረገ ማለት ነው። ሥነ ፍጥረት መፈጠር ከጀመረ አራተኛ ቀን ስለሆነ ረቡዕ ተብሏል።
- እግዚአብሔር ሶስት ፍጥረታትን የፈጠረ ሲሆን "በጠፈር ላይ ብርሃን ይሁን" ዘፍ፤ 1፣12 ብሎ ሲያዝ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጥረዋል።
- ፀሐይ ከእሳትና ከነፋስ የተፈጠረች ሲሆን ከእነዚህ ፍጥረታት መፈጠሯ በምን የታወቃል? ቢሉ ከእሳት ለመፈጠሯ ታተኩሳለች / ታቃጥላለች/ ከነፋስ ለመፈጠሯ ትሔዳለች።
- በመቀጠል ከውሃና ከነፋስ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጥሯል። ይህስ በምን ይታወቃል? ቢሉ በነፋስነታቸው ይሄዳሉ፣ በውሃነታቸው ይቀዘቅዛሉ።
- እነዚህ ብርሃናት የተፈጠሩበት ዋናው ዓላማ "- መዓልቱን ከሌት፣ ሰዓቱን ከዕለት፣ ዓመቱን ከዘመን ለመለየት ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ሹሟቸዋል።" እንዲል ኩፋሌ፤ 2፣13

# ከዕለተ ረቡዕ ፍትረታት ምን እንማራለን?

- **በዕለተ ረቡዕ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንማራለን።**

- ፀሐይ ሁልጊዜ ሙሉ ስለሆነች የጻድቃን ምሳሌ ናት።ጻድቃን በምግባር በሃይማኖት ዘወትር ምሉዕ /ሙሉ/ ናቸው።

- ጨረቃ አንድ ጊዜ ስለምትሞላ አንድ ጊዜ ስለምትጎድል የኃጥአን ምሳሌ ናት። ኃጥአን በምግባርና በሃይማኖት አንድ ጊዜ ሲሞሉ አንድ ጊዜ ሲጎድሉ ይኖራሉ። "-የሃጢአተኛ ልብ እንደ ጨረቃ ሲጎድል ያድራል" እንዲል ሲራክ፤ 43፥7

- አንድም ፀሐይ የኃጥአን ምሳሌ፣ ጨረቃ  የጻድቃን ምሳሌ፤ ጸሐይ ሁልጊዜ ምሉዕ እንደ ሆነች ሁሉ ኃጥአንም በክፋ ስራቸው፣ በክፋ ምግባራቸው፣ በክህደታቸው ምሉዓን ናቸው። ጨረቃ አንድ ጊዜ ስትሞላ አንድ ጊዜ እንደምትጎድለው ሁሉ ጻድቃንም በኃጢአት አንድ ጊዜ ሲወድቁ ሌላ ጊዜ በንስሐ ሲነሱ ይኖራሉ። "- ጻድቅ ሰው ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ ይነሳል፡፡" ምሳሌ፤ 24፥16

- ሰስቱም ብርሃናት ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ሲወጡ ሲገቡ ፊታቸውን ወደ ምስራቅ አድርጎ ፈጥሯቸዋል። እንደዚሁም ሁሉ ምዕመናን ፊታቸውን ወደ ምስራቅ አዙረው ለመጸለያቸው ምሳሌ ነው። ጨረቃ ሰርቅ ካደረገች በኋላ ለአስራ አራት ቀናት

# የሐሙስ ስነ ፍጥረት

- ሐሙስ የሚለው ሐመሰ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን አምስት አደረገ ማለት ነው። ለሥነ ፍጥረት አምስተኛ ቀን ስለሆነ ሐሙስ ተብሏል።
- በዚህ ቀን እግዚአብሔር " ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾችን ታስገኝ፣ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ይብረሩ።" ዘፍ፤ 1፣20
- "- እግዚአብሔርም ታላላቅ አንበሪዎችን ውሃይቱ እንደወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ።" ዘፍ፣ 1፣21 በዚህን ጊዜ፡-
- · በእግር የሚሽከረከሩ፣
- · በልባቸው የሚሳቡ፣
- · በክንፋቸው የሚበሩ አድርጎ ሶስት ፍጥረታትን በደመ ነፍስ ሕያዋን የሆኑ ከባሕር ፈጠራቸው።

# ምሳሌነታቸውም፡-

- 1ኛ. በባሕር ውስጥ ጸንተው የሚኖሩት፡- በእምነታቸው ጸንተው፣ በእግዚአብሔር አምነው የሚኖሩ ምሳሌ፣ አንድም በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው በትዳር ተወስነው በሀብት በንብረታቸው መልካም ስራ እየሰሩ ማለትም ለቤተ እግዚአብሔር አንጽፈው፣ መስዋዕት አቅርበው፣ አስራታቸውን /ከደሞዛቸው ከአስር አንድ / በኩራታቸውን /ከሰውና ከእንስሳ በመጀመሪያ የተገነውን ለቤተ እግዚእብሔር ለግሰው/ ቀዳማያት/ከሰብላቸው፣ ከአዝርዕታቸው ቀዳሚውን ሰጥተው/ የሚኖሩ በሕግ ጋብቻ ተወስነውና ጸንተው ሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ፣ አንድም ክፉ ግብራችንን አንተውም ብለው በመስረቅ፣ በመቀማት፣ ቋንጃ በመቁረጥ፣ ነፍስ በማጥፋት፣ በመዘሞት ጸንተው የሚኖሩ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው።

- 2ኛ. ከባሕር ወጥተው የቀሩት - ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" በሚለው ቃል ተማርከው ይህን ዓለም በመናቅ ከዘመድ ባዳ፣ ከሀገር ምድረ በዳ ከሕገ ሰብእ ሕገ መላዕክት፤ ከተግባረ ስጋ ተግባረ ነፍስ ይሻለናል ብለው ይህን ዓለም ንቀው በገዳማት በሰድባራት ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ የሌሊት ቁሩን የቀን ሐሩር፣ ግርማ ሌሊቱን፣ ድምጸ አራዊቱን ታግሰው ዳባ ለብሰው፣ ዳዋ ጥሰው፣ ከደል ወድቀው፣ ከዛፍ ስር ተጠግተው የሚኖሩ የመናንያን መነኮሳት ምሳሌ ነው። ዕብ፤ 11፣35

- 3ኛ. አንዴ በባሕር አንዴ በየብስ ወጣ ገባ እያሉ የሚኖሩት · አንድ ጊዜ ወደ ገዳም፣ ዕጸበ ገዳም ሲያስቸግራቸው እንድ ጊዜ ወደ ዓለም ወጣ ገባ እያሉ የሚኖሩ የመነኮሳት ምሳሌ፣ · አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት አንድ ጊዜወደ ክህደት የሚሄዱ የምዕመናን ምሳሌ፣

# ይቀጥላል--

- ከዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት ምስጢረ ጥምቀትን እንማራለን።
- በባሕር ጸንተው የሚኖሩ፡- በጥምቀተ ክርስትና አምነው ተጠምቀው የሚኖሩ ምሳሌ ናቸው። "- ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያያት አይችልም።" ዮሐ፤ 3፣5 "- ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል።" ማር፤ 16፣16
- ከባሕር ወጥተው የቀሩት፡- በጥምቀተ ክርስትና አምነው ተጠምቀው ሲያበቁ በተለያየ ምክንያት ማለትም በፈተና፣ በምንፍቅና፣ በክህደት፣ ለዚህ ዓለም ባለጸግነት ብለው ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅጸነ ዮርዳኖስ ያገኙትን የእግዚአብሔር ልጅነታቸውን፣ የተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን የሚያጡ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።
- አንድ ጊዜ ከባሕር አንድ ጊዜ በየብስ የሚኖሩ፡- በጥምቀት ያገኙትን የእግዚአብሔር ልጅነት በደንብ ተረድተው ያልያዙ፤ ሲላቸው በሃይማኖት ሲያሻቸው በክህደት የሚኖሩ፤ ባካና ልቡና ይዘው እንደ ሁኔታው የሚቀያየሩ፤ በደግ ጊዜ በሃይማኖት የሚኖሩ፣ ፈተና ሲመጣ ፈተናውን ለማለፍ በሚል ሰበብ የሚክዱ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።

# የዓርብ ስነ ፍጥረት

- ዓርብ ዐረበ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ተካተተ ማለት ነው። ስለዚህ ዓርብ ማለት መካተቻ መደምደሚያ ማለት ነው።
- ዐርብ የተባለበት ምክንያት በዕለተ እሑድ መፈጠር የጀመሩት ፍጥረታት ተፈጥረው ያበቁበት /የተካተቱበት/ ቀን ስለሆነ ዐርብ ወይም መካተቻ ተብሏል። ዕለተ ዓርብ ለሥነ ፍጥረት ስድስተኛ፣ ለጥንተ ቀመር አምስተኛ፣ ለጥንተ ዮን አራተኛ ቀን ነው።
- በዚህ ቀን እግዚአብሔር "- እግዚአብሔር አለ፦ ምድር ሕያዋን ፍጥራታትን እንደ ወገኑ እንስሳትን ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ።" ዘፍ፤ 1፣24
- በዚህን ጊዜ ሶስት ፍጥረታት በየወገናቸው ተፈጥረዋል። እነዚህም ልክ እንደ ሐሙስ ፍጥረታት በእግር የሚሽከረከሩ፣ በልብ የሚሳቡ እና በክንፍ የሚበሩ ናቸው።
- በዚህ ቀን በአራተኛ አዳምን ፈጥሯል።

# ይቀጥላል--

- “ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር” በማለት አራቱን ባሕርያተ ሥጋና ሶስቱን ባሕርያተ ነፍስ አዋሕደው አዳምን ፈጠሩት።

# ይቀጥላል--

- በመልካችንና በአምሳላችን እንፍጠር ማለታቸው ለሥላሴ እንደ ሰው ግዙፍ የሆነ አካል ባይኖራቸውም ረቂቅ በሆነው አካላቸው ላይ በሰው ላይ ያለው መልክ አላቸውና ነው።
- አንድም ሥላሴ ዘላለማውያን ስለሆኑ አዳምም የማትሞት ሕያዊት የሆነች ነፍስ ስላለው ነው።
- አንድም በአንድነትና በሶስትነት ይመስላቸዋልና ነው። ሥላሴ ለባውያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን እንደሆኑ ሁሉ አዳምም ነባቢት፣ ለባዊት፣ ሕያዊት ነፍስ አለው።
- ሥላሴ ለባውያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን ቢሆኑም ሶስት አማልክት አይባሉም። እንደዚሁ ሁሉ አዳምም ለባዊ፣ ነባቢ፣ ሕያዊ ስለሆነ ሶስት ሰው አይባልም። አንድ ሰው ይባላል እንጂ።
- አዳም ማለት ያማረ፣ የሰመረ፣ የተዋበ፤ እንደ ረዓይት / እጅግ በጣም ሳይረዝም፤ እንደ ድንክ ሳያጥር የተፈጠረ፤ ይህ ቀረህ የማይባል እጅግ መልከ መልካም ማለት ነው። አንድም - ከመሬት የተገኘ /ሰው የሆነ/ ማለት ነው።

# ይቀጥላል--

- ሃያ አንዱን ፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ እርሱን ሃያ ሁለተኛ አድርጎ በመጨረሻ ለምን ፈጠረው?
- አንድ ሰው እቤቱ እንግዳ ሲጋብዝ አስቀድሞ የሚበላውን፣ የሚጠጣውን አዘጋጅቶ ነው እንጂ እንግዳው ከገባ በኋላ አይደለም ማዘጋጀት የሚጀምረው። እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔርም ለአዳም የሚያያስፈልገውን የሚበላውን፣ የሚጠጣውን፣ የሚገዛው፣ የሚነዳውን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ፈጠረው።
- ሌሎችን እንስሳት ስንመለከት ሁሉም ጎንበስ ብለው የተፈጠሩ መሆናቸውን እናስተውላለን፤ ነገር ግን አዳምን ቀና አድርጎ ከሌሎቹ ለይቶ ፈጥሮታል።
- አዳምን ገዢ፣ ሌሎችን ተገዢ ናችሁ ሲላቸው፤ አንድም አዳም ሞቶ፣ ፈርሶ፣ በስብሶ አይቀርም ከሞት በኋላ ትንሳኤ አለው፤
- አዳም በተፈጠረ በስምንተኛው ቀን፣ በሶስት ሰዓት ሔዋን ተፈጠረች። "- አዳምን ብቻውን ይኖር ዘንድ አይገባውም ረዳትን እንፍጠርለት" ዘኍ፤ 2፣18 ።
- ሁለቱም ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው ለሰባት ዓመታት ከቆዩ በኋላ በምክረ ከይሲ ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሰው ከገነት ተባረዋል።

# Revision

- The following Slides contain Questions for Revision

# ሥነ ፍጥረት ምን ማለት ነው?

- ሥነ ፍጥረት ከሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን ሥን ማለት ያማረ፣ የሰመረ ማለት ሲሆን ፍጥረት ደግሞ የተፈጠረ ወይም የተገኘ ማለት ነው። ሥነ ፍጥረት ያማረ፣ የሰመረ የተዋበ ፍጥረት ማለት

# የሥነ ፍጥረት አስገኚ ማን ነው?

- ሥነ ፍጥረት አንድ ጊዜ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው።
- ቅዱስ ዮሐንስ "ሁሉም በእርሱ ሆነ/ተፈጠረ/፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" ዮሐ፤ 1፣3 እንዳለው።
- ቅዱስ ጳውሎስ "ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ስለዚህ የሚታየው ነገር ከሚታየው እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።" ዕብ፤ 11፣3 ።

# እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ለምን ፈጠረ?

- · ሰውና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ፣ ክብሩን ለመልበስ፣ መንግስቱን ለመውረስ፤
- · ሰማይና ምድርን ለፍጥረታት ማደርያ፤
- · አራቱን ባሕርያት /እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስና መሬት/ ለፍጥረት መገኛ፤
- · ሌላውን ፍጥረት ለአንክሮ / እንዲደነቅበት/፣ ለተዘክሮ/ አምላክ መኖሩን ለማሳሰብ/ ለምግበ ሥጋ፣ ለምግበ ነፍስ ፈጥሯቸዋል።

# በዓለም ውስጥ ያሉ ፍጥረታት ስንት ናቸው?

- በየወገኑ፣ በየወገኑ፤ ብዙውን አንድ፣ ብዙውን አንድ አድርገን ስንቆጥር ሃያ ሁለት ናቸው። አዳም በገነት እያለ ይጸልይባቸው የነበሩ በኋላም ቅዱስ ዳዊት በመዘሙሩ ያነሳቸው ስመ አምላክ /የአምላክ ስሞች ሃያ ሁለት ናቸው። እነዚህም “አሌፍ፣ ቤት፣ ጋሜል፣ ዳሌጥ፣ ዋው፣ ዛይ፣ ሔት፣ ጤት፣ … ታው” መዝ፤ 118፣1

የሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት መገኛ ፍጥረታት የተፈጠሩት በሁለት መንገድ ሲሆን እነሱም፡-

- · ከምንም ምን ወይም በባዶ፡- ሰባተት ፍጥረት ሲሆኑ እነሱም እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስ፣ መሬት፣ ጨለማ፣ ሰባቱ ሰማያት እና መላዕክት ናቸው።
- · ፍጥረት እምፍጥረት፡- እነዚህ ከአንድና ከዚያ በላይ ከሆኑ ፍጥረታት የተፈጠሩ ሲሆኑ ከላይ
- ከተጠቀሱት ሰባቱ ፍጥረታት ውጪ ሌላው አስራ አምስቱ በዚህ መልክ የተፈጠሩ ናቸው። መገኛቸውም ከአራቱ ባሕርያት / ከእሳት፣ ከውሃ፣ ከነፋስና ከሬት/ የተፈጠሩ ናቸው።

# ፍጥረታት ሲፈጠሩ በሶስት ዓይነት ሁኔታ ነው፡-

- · በአርምሞ ፡- በዝምታ ወይም ባለመናገር ሲሆን በአርምሞ የተፈጠሩ ሰባት ፍጥረታት ናቸው። እነሱም፡- አራቱ ባሕርያት፣ ጨለማ፣ ሰማያትና መላዕክት ናቸው።
- · በነቢብ /በመናገር/፡- በመናገር የተፈጠሩ አስራ አራት ፍጥረታት ሲሆኑ እነሱም ከብርሃን ጀምሮ ያሉ አስራ አራቱ ፍጥረታት ናቸው።
- · በገቢር / በመስራት /፡- በገቢር የተፈጠረው ሃያ ሁለተኛው ፍጥረት አዳም ብቻ ሲሆን ከምድር አፈር አበጃጅቶ በሰባት ባሕርያት አጽንቶ ፈጥሮታል። ዘፍ፤ 2፣7

# ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት)

የቤተ ክርስቲያን መሠረቷና ሀብቷ በእግዚአብሔር የተሰጣት ሃይማኖት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ አካላት ሆነው የተሠሩትንና በመሠረት ላይ ያሉትን ምእመናን አንድ የሚያደርጋቸው ይህ ሃይማኖት ሲሆን አንድነታቸው የሚገለጠው ደግሞ በሱታፌ ምሥጢራት አማካይነት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከተሰጣት ሃይማኖት ደግሞ ነገረ ድኅነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥጋዌ ጋር መሠረቷና ጉልላቷ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሌሎች የእምነት ድርጅቶች

መዳን የሚለው ቃል እንደ አገባቡ የተለያየ መልእክት ወይም ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል መዳን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተለያዩ ዓይነት ችግሮችና ጥፋቶች ስለ መዳንና ነጻ ስለ መሆን ተነግሮ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌም፡- ኖኅ ከጥፋት ውኃ መዳኑ (ዘፍ. 6-9)፣ ሎጥ በሰዶምና በገሞራ ላይ ከደረሰው የእሳትና የዲን ቃጠሎ መዳኑ (ዘፍ. 19)፣ ያዕቆብና ልጆቹ ዮሴፍ አስቀድሞ ወደ ግብጽ በመሄዱ ምክንያት በዘመኑ ከነበረው ከባድ ረሃብ መዳናቸው፣ ንዕማን ሶርያዊ ከነበረበት ለምጽ በዮርዳኖስ ወንዝ ታጥቦ መዳኑ፣ ሕዝበ እስራኤል ከሐማ ተንኮል

"ፈውስ" ተብለው የሚጠሩ ናቸው፡፡ በነገረ ድኅነት ትምህርት "መዳን" ስንል ግን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሱ ምክንያት የደረሱበትን ተደራራቢ ውድቀቶች፣ ቅጣቶች፣ ከጸጋ መራቆቶችና የባሕርይ መጎሳቆሎች እና ኋላም በእግዚአብሔር ልዩ ምክር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን መዳን ማለታችን ነው፡፡

የመዳን ትምህርት ከትምህርቶች ሁሉ ዋናውና የመጀመሪያው ነው። ምክንያቱም የክርስትና ሃይማኖት የመዳን ሃይማኖት ስለሆነ ነው። ከዚሁም ጋር የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ሕይወቱን በተመለከተ የማያቋርጥ ውሳጣዊ ፍለጋና ሕሊናዊ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ በመጀመሪያ ሊመለስለትና ሕሊናውን ሊያሳርፍበት የሚገባው ጉዳይም ይኸ በመሆኑ ነው። የሰው ልጅ የሚኖረው በዚህ ዓለም ላለው ለጥቂቱ ዘመን ብቻ ሳይሆን ከዘመን ውጭ ለሆነው ዘለዓለማዊነት ስለሆነና ሊሆንም ስለሚገባው ነው። የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት) እንዲህ የመኖራችን ዓላማና የክርስትና ምንነትና መሠረት ስለሆነ የትምህርት ሁሉ መዓዝን ነው። አስተምህሮዎችና አስተሳሰቦች ሁሉ የሚመዘኑትና የሚለኩት በነገረ ድኅነት መለኪያነትና ሚዛንነት ነው። የመናፍቃን ኑፋቄም

# መዳን ለምን አስፈለገ?

እንድ ነገር "መዳን" ያስፈልገዋል ሲባል በችግር ላይ የነበረና መዳንን ገና ያላገኘ መሆኑን ያመለክታል። ስለ ሰው ልጅ መዳን ስንናገርም ከሁሉ አስቀድሞ መዳን ለምን አስፈለገው? የሚድነውስ ከምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሣት የግድ ይሆናል። ሰው ለምን መዳን አስፈለገው? ሲባል መልሱ ሰው በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት ትቶ ዲያብሎስን አምኖ ሕግ እግዚአብሔርን አፍርሶ ትእዛዙን ጥሶ የተሰጠውን ሕይወት፣ ጸጋና ክብር በራሱ ጥፋት በማጣቱና ከሕይወት ወደ ሞት፣ ከክብር ወደ ኃሳር ወርዶ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ለሌሎች ፍጥረታት ያላደረገውን ልዩ ነገር በማድረግ፣ ይኸውም "ንግበር ሰብአ በአርአያ ወበአምሳሊነ - ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" በማለት በራሱ መልክና ምሳሌ ፈጠረው፡፡ እንዲሁም ሰውን በሕያዊት ነፍስ አክብሮ፣ ነጻነት ያለው፣ ክፉውንና በጎውን መለየትና መምረጥ የሚችል፣ አዋቂና አስተዋይ አድርጎ ፈጠረው፡፡ ስለዚህም ይረዳው ዘንድ ክፉ እውቀትን ወደ ማወቅ እንዳይሄድና የሚኖረው እውቀት ምን ጊዜም መልካም የሆነ፣ የማይጎዳና የማያስጸጽት ብቻ ይሆንለት ዘንድ "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" በማለት አዘዘው፡፡ ይህ የሕግ ምልክትም የሰው ልጅ ለፈጣሪው ያለውን ፍቅሩን ይገልጽበት ዘንድ የተሰጠው መንገድ ነበር፡፡ ዘፍ. 2፥16-17 ሆኖም የሰው ልጅ ይኸን ሁሉ ቸርነት ካደረገለት ከእግዚአብሔር ይልቅ ምንም ነገር ያላደረገለትንና ባዶ የሆነ የቃል ተስፋ ብቻ ይዞ የመጣውን ዲያብሎስን በማመን በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ አምላኩን ካደ፤ በፈጣሪው ላይ ላለው እምነትና ፍቅር መግለጫ የነበረውን ምልክትም አፈረሰ፡፡

የአዳም የመጀመሪያውና ዋናው ኃጢአቱ (በደሉ) ቅጠል ቆርጦ መብላቱና አለመታዘዙ ሳይሆን እግዚአብሔርን አለማመኑ ነበር፡፡ አለመታዘዙ የመጣው ካለማመኑ ነበር፤ ማለትም አዳምን የፈጣሪውን ትእዛዝ ወደ መጣስና ሕጉን ወደ ማፍረስ የወሰደው በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነት በዲያብሎስ ስብከት ከተለወጠ በኋላ ነበር፡፡ ከመነገር በላይ የሆነውን መልካሙን ሁሉ

ምክንያት የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር የመለየቱ ውጤት የሆኑ ብዙ ተደራራቢ ነገሮች ደረሱበት፡፡ እነዚህም በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ሞት፡ ሟችነት

ሰው የተፈጠረው ለሕይወት እንጂ ለሞት አልነበረም፡፡ ሆኖም ሰው ሲፈጠር እንደ መላእክት ከመጀመሪያው የማይሞት ተደርጎ አልተፈጠረም፤ ነገር ግን ሕጉን ቢጠብቅ በሕይወት ሲኖር፣ ባይጠብቅ ደግሞ ሊሞት እንዲችል አድርጎ በግዕዛናዊ ሁኔታ ነበር እግዚአብሔር የፈጠረው፡፡ ማለትም ወደ ወደደው መንገዝ ይችል ዘንድ በሟችነትና በኢሟችነት መካከል አድርጎ ፈጠረው፡፡ ሕጉን ለተወሰነ ጊዜ (እግዚአብሔር ለሚያውቀው ጊዜ) ቢጠብቅ ወደ ኢሟችነት ሲሸጋገር፣ ባይጠብቅ ደግሞ ወደ ሟችነት ሊወርድ በሙሉ ነጻነት ተፈጠረ፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ቸርነት ነበር፡፡ ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው ኢሟች (ለምሳሌ እንደ መላእክት የማይሞት) ተደርጎ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ አንደኛ ሊሞት የሚችል ሆኖ ተፈጥሮ እያለ እንኳ እንደዚያ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጽና የሚክድ ከሆነ ከመጀመሪያውኑ የማይሞት ተደርጎ ቢፈጠር ኖሮ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ከባድ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ከመጀመሪያው ኢሟች ሆኖ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ኃጢአት ሲሠራ ኃጢአቱ ከባሕርዩ ጋር ተዋሕዶ ለዘለዓለም የባሕርዩ አካል ሆኖ ስለሚኖር "የማይሞት ሞት" ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ይህም ባሕርዩ ጎስቋላ እንደ አጋንንት መጨረሻ የሌለው ሞት በሆነበት ነበር፡፡

ሰው መሞት የሚችል ሆኖ በመፈጠሩ ወደ ባሕርዩ ውስጥ ዘልቆ የገባው ኃጢአት የባሕርዩ ዘለዓለማዊ አካል ሳይሆን ከእርሱ የሚወገድበትን መንገድ - ሞትን - አዘጋጀለት፡፡ በበደለ ጊዜ በሰው ላይ ሞትን ማዘዙ በራሱ የእግዚአብሔር የቸርነቱ ሥራ ነበር፡፡ በዚህም ወደ ውስጣችን ዘልቆ የገባው ኃጢአት በሞት ከእኛ ይለያል፤ እግዚአብሔር የፈጠረውና በሐዲስ ተፈጥሮ ያከበረው ሰውነታችን ደግሞ በትንሣኤ በክብር ይነሣል፡፡ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ኢሟች ያላደረገን በዚህ ቸርነቱ ምክንያት ነበር፡፡ ሆኖም ግን በመጀመሪያ የተሰጠንን ዕድል - ኢሟችነትን - ገንዘብ ማድረግ እንችል ዘንድ የሕግን ምልክትነት ሰጠን፡፡ ሆኖም ግን ያን የተሰጠንን መንገድ ራሳችን አበላሸነው፤ ሳንጠቀምበትም ቀረን፡፡

## 2. የባሕርይ መጎስቆል ደረሰበት

የሰው ባሕርይ እጅግ ግሩም በሆነ ሁኔታ በክብር የተፈጠረ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ብርሃን አልብሶ በጸጋ አጎናጽፎ በአርአያውና በምሳሌው አስውቦና አክብሮ እንደ ፀሐይ በሚያበራ ብርሃናዊ ጸዳል ይህ ቀረው በማይባል ክብርና ጸጋ ነበር፡፡ ነገር ግን ሕግን በማፍረሱ ምክንያት ባሕርዩ ጎሰቆለ፣ ተዋረደ፡፡ ጸጋውን ተገፍፎ ራቁቱን ሆነ፣ ቅጠል ሰፍቶ አገለደመ፣ ቁርበት ለበሰ፡፡ ክብሩን በማጣቱ ምክንያት ከእርሱ ያነሱ ሥነ ፍጥረቶች ተገዛ፣ እነርሱን መፍራትና ማምለክም ጀመረ፡፡ "ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ - ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም፣ አእምሮ እንደ ሌላቸው እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" እንደ ተባለው ሆነ። መዝ. 48፥12

## 3. ስደተኛ ሆነ

ክቡታው ከገነት ተባረረ፤ የራሱ ኃጢአት አሳደደው፡፡ ቀድሞ የደስታው ምንጭ የነበረው የእግዚአብሔር ድምጽ አሁን ግን አስፈራው፡፡ ስለዚህም ከእግዚአብሔር ሸሸ፤ ለመሸሸግም ሞከረ፡፡ እግዚአብሔር "ወዴት ነህ?" ብሎ በጠራውና በፈለገው ጊዜ "በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም" በማለት እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ መለሰ፡፡ ዘፍ. 3፥9-10 እግዚአብሔርም የበደለውን አዳምን ቀናና በመስጠት ከገነት አስወጣው፡፡ "እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፤ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።" ዘፍ. 3፥23-24 ስለዚህም ግዞተኛ ሆኖ ወደ ምድር ተጣለ፡፡

## 4. ሰላም አጣ፤ ተጨነቀ

የሰው ልጅ የሰላም አምላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር በመለየቱ ምክንያት የሚፈራ፣ የሚደነግጥ፣ የሚጨነቅ፣ የሚታወክ ሆነ። ከመበደሉ በፊት የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት የደስታው ምንጭ ነበር። "ኃጥእን ሰው ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፤ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል" እንደ ተባለ ሰውን ኃጢአቱ አጠመደው፣ አሰረውም። ምሳ. 5፡22 የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰላም መስማት አልቻለም፤ ድምፁን ሲሰማ ሥራው ትዝ እያለው ይፈራና ይሸሽ ጀመር። "ለክፉዎች ሰላም የላቸውም" እንደ ተባለ የራሱ ክፉት ሰላሙን አሳጣው። ኢሳ. 48፡22

## 5. መንፈሳዊ እድገቱ ተቋረጠ፤ መቋረጥ ብቻም ሳይሆን ጉዞው በተቃራኒ አቅጣጫ ሆነ።

ሰው ሲፈጠር በቅድስናና በጸጋ እያደገ መሄድ እንዲችል ሆኖ ነበር የተፈጠረው። ከውድቀቱ በኋላ ግን እንደ ተነቀለ ችግኝ ያ ዕድገቱ ተቋረጠ። መልካም የሆነው የመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገት መቋረጥ ብቻም ሳይሆን የሕይወቱ አቅጣጫ የሚጓዘው በተቃራኒ አቅጣጫ ሆነ። ሕይወቱ ወደ ተቃራኒ የጥፋት አቅጣጫ (ወደ አለ መኖርና ወደ ጥፋት አቅጣጫ) መውረድ ጀመረ። ሂደቱ ከመከራ ወደ መከራ፣ ከውርደት ወደ ውርደት ሆነ።

## 3.2 ሰውን ሊያድነው የሚችለው ማን ነበር?

ለሰው ልጅ ወደ ባሕርዩ ውስጥ ዘልቆ የገባውን ሞት አስወግዶ ሕይወትን የሚሰጠው፡ ያጣውን ሰላምና ነጻነት የሚመልስለት፡ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን አንድነት ሊመልስለት የሚችለው ማን ነበር?

1. ሰው መሆን አለበት፡ ምክንያቱም የበደለው ሰው ነውና፤

   የበደለውና የተፈረደበት ሰው ስለሆነ አዳኙም ሰው ካልሆነ ማዳኑና አፈጻጸሙ የተገጣጠመ አይሆንም፡ ይዛነፋል፤ ችግሩና መፍትሔው በትክክል አይገጣጠሙም፡፡ የበደለው ሰው ሆኖ ሳለ ሌላ ተገብቶ ቢያድነው እግባብነቱ ሙሉ አይሆንም፡፡

2. መሞት አለበት፡ በበደለኛው ላይ የተፈረደበት ቅጣት ሞት ነውና፡

በበደለው በሰው ላይ የተፈረደው ፍርድ ሞት ስለሆነ ("በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ተብሎ) ያ ዕዳ ካልተከፈለ በስተቀር ሰው ነጻ ሆነ፡ ዳነ ማለት አይቻልም፡፡ ወይም ደግሞ ይህ ፍርድ ሳይፈጸም ቢድን የእግዚአብሔር ቃል ተፈጻሚነት ጉዳይ ችግር ላይ ይወድቅ ነበር፡፡

3. ሞትን ማሸነፍ መቻል አለበት፤

ሰውን የሚያድነው መድኃኒት መሞት መቻል ብቻ ሳይሆን ሞትንም ማሸነፍ የሚችል መሆን ነበረበት፡፡ አለበለዚያ መሞቱ ብቻ ለሰው ልጅ የሚጠቅመው ነገር አይኖርም ነበር፡፡ ሞትን መቀበል መቻልና መሞት ብቻ ሳይሆን ሞቶ ሞትን ድል ማድረግና ማሸነፍ መቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም ሞትን ድል ማድረግ ካልቻለ እንዲሁ ቢሞት የሚቾችን ቁጥር በአንድ ከመጨመር በስተቀር በመሞቱ ብቻ የሚያስገኝልን ጥቅም አይኖርም ነበርና፡፡

4. ንጹሐ ባሕርይ መሆን አለበት፤

ስለ ኃጢአተኞች ለመካስ ሚቹ ከበደልና ከኃጢአት ዕዳ ንጹሕ መሆን ይኖርበታል፡፡ ራሱ ንጹሕ ካልሆነ ቢሞት እንኳ በራሱ ዕዳ ይሞታል እንጂ ለሌሎች ቤዛ ሊሆን አይችልምና፡፡

## 3.6 መዳን (ድኅነት) - የእግዚአብሔር ስጦታ? ወይስ የሰው የሥራው ውጤት?

እግዚአብሔር የሰጠን የመዳን ጸጋ የቸርነቱ ስጦታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠን መዳን ከሰዎች መልካምነት ወይም ከተጋድሎ የተነሣ የተገኘ አይደለም፤ ከፍጹም ቸርነቱ የተነሣ የተሰጠን ጸጋ ነው እንጂ፡፡ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ሰው የዳነው በእግዚአብሔር ቸርነት (ጸጋ) ነው፡፡ የሰው ድኅነት የእግዚአብሔር የቸርነቱ ስጦታና ለሰው ያለው የማይለወጥ ፍቅር ውጤትና መገለጫ ነው፡፡ ድኅነታችን የተገኘው በእኛ ሥራ መልካምነት አይደለም፡፡ በአንድ በኩል የሰው ልጆችን አጠቃላይ የቀደመ ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳነን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡-

> እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፡ እንደ ሌሎችም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጸጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና፡፡ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡ ኤፌ. 2፡3-8

## 3.7 ለመዳን እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

ለመዳን የሰው ልጅ ድርሻ ለዚህ የእግዚአብሔር ስጦታ በጎ ምላሽ መስጠትና ድኅነትን ያገኘበት ዘንድ በተነገረው መንገድ መሄድና መዳንን ገንዘብ ማድረግ (የራሱ ማድረግ) ነው፡፡ በእግዚአብሔር በኩል ሰውን ለማዳን አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ - የእግዚአብሔር ድርሻ - ተፈጽሟል፡፡ ስለ እያንዳንዳችን መዳን በእግዚአብሔር በኩል ያልተፈጸመና የቀረ አንድም ነገር የለም፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዳናችንን በሥጋዌው ፈጽሟል፡፡ አሁን የሚቀረው የእያንዳንዳችን ድርሻ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሠርጉን ደግሶ የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጅቶ "ሁሉም ተዘጋጅቷል፤ ወደ ሠርጉ ኑ በሏቸው" በማለት እየጠራ ነው። ማቴ. 22፡4 የእግዚአብሔርን ጥሪ "እሺ" ብሎ ተቀብሎ የሠርግ ልብስ ለብሶ ወደ ሠርጉ ቤት መግባት ደግሞ የእያንዳንዱ ድርሻ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ የእያንዳንዱን ሰው ፈቃድና ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

በመዳናችን ላይ የእኛ ድርሻ የልባችንን በር ለሚያንኳኳው ጌታ በራችንን መክፈት፣ ድንጋዩን ከመቃብሩ ላይ ማንሣት ነው፡፡ ዋናው የእግዚአብሔር ነው፤ ሆኖም የሰውን ድርሻ ጨርሶ የሚያጠፋና የሰውን ነጻ ፈቃድ ከንቱ የሚያደርግ "መዳን" በኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት ተቀባይነት የለውም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና፡፡ መዳን በአንድ ሰው ላይ ያለ ፍላጎቱ የሚጫን ግዴታ አይደለም፡፡ በመዳናችን የተመለሰልን አንዱ መሠረታዊ ነገር ጨርሶ ባይጠፋም በውድቀታችን ምክንያት ደክሞና ፈዝዞ የነበረው ነጻነታችን ነውና፡፡ ስለዚህ በጥምቀት የመዳናችን ዘር ይዘራል፤ በሌሎቹ ምሥጢራት እያደገና ፍሬ እያፈራ ይሄዳል፤ ይህም እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ በኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መዳን በአንድ ቅጽበት ተፈጽሞ ከዚያ በኋላ "ድኛለሁ" እያሉ የሚፎከርበት ሳይሆን ሐዋርያው "ስለዚህ፤ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁል ጊዜ እንደ ታዘዛችሁ . . . በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" በማለት እንዳስተማረን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በትጋት እስከ መጨረሻው በመጽናት የሚፈጸም ነው፡፡ ፊል 2፥12 ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈላቸው የፊልጵስዩስ ሰዎች ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ታዲያ መዳናቸው ተፈጽሞ አልቆ የነበረ ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ክርስቲያኖች የሆኑትን ምእመናን መዳናቸው ገና ያልተፈጸመ ይመስል "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" ለምን አላቸው?

ሰውን ያዳነው የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ይህን መዳን ለመፈጸምና በተሰጠው የመዳን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ ነገር አለ፡፡ ሐዋርያው የእግዚአብሔርን የማዳን ነገር ሲገልጽ፡- "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው" በማለት ንጹሐ ባሕርይ የሆነ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት "ኃጥእ" ተብሎ መከራ በመቀበሉ የእኛ ኃጢአት መወገዱንና በእርሱ "ኃጥእ" መባል እኛ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" መሆናችንን ገለጸ፡፡ በመቀጠልም "አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን" አለ፡፡ 2 ቆሮ. 5:21 ፤ 6:1 ይህም ማለት እግዚአብሔር ያደረገልንን የማዳን ጸጋ ለመቀበል ከእኛ የሚጠበቀውን ነገር (ምንም እንኳ የምናደርገው ነገር ለጸጋው ምንም የማይመጥንና እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም) ሳናደርግ እንዳንቀር ነው፡፡ ይህም እያንዳንዳችን ማድረግ ያለብን የራሳችን ድርሻ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ከእርሱ የሚጠበቅበትን ለማይፈጽም ሰው የእግዚአብሔር ሰውን ማዳን ብቻ በራሱ እንዲድን አያደርገውም፡፡

እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የሚከተሉትን መፈጸም ይኖርበታል፡፡

### 3.7.1 እምነት (ማመን)

ማመን ማለት በዋናነት እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን በፈቃዱ ያደረገውን ነገር ሁሉ ማመንና መቀበል (እምነት) እና በአጠቃላይ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም በሥጋዌው የገለጸውን የእውነት ትምህርት (ሃይማኖት) ሳይቆነጻጽሉና ሳያጎድሉ በምልአት መቀበልና ማመን ነው፡፡

ማመን ስንል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን፣ በአንድነቱ ውስጥ ልዩና የማይመረመር ሦስትነት ያለው መሆኑን፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው መሆኑን፣ ሥግው ቃል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመወለድ ጀምሮ ለሰው ሲል ያደረውን - መጠመቁን፣ ዞሮ ማስተማሩንና ያስተማረውን ቃልና ትእዛዝ ማመንን፣ መከራ መቀበሉን፣ በመጨረሻም በራሱ ፈቃድ ለእኛ ሲል መሞቱን፣ መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን መነሣቱን እና በአርባኛው ቀን ወደ ቀደመ ክብሩ ማረጉን . . . ሁሉ ማመን ለመዳን አስፈላጊ ነው፡፡

እንዲሁም "የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፣ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፤ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ" በማለት እምነት እርሱ የነገረንን ቃል መቀበልና ማመን መሆኑን ተናግሯል፡፡ ዮሐ. 17፡8 በአጠቃላይ እግዚአብሔር እርሱን ማወቅ በምንችለው መጠን እናውቀውና እናምነው ዘንድ፣ ወደ እውነት ይመራን ዘንድ በቅዱስ መጽሐፍ የገለጠውን እውነት መቀበልና ማመን ለድኅነት የግድ ነው፡፡ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፣ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" እንደ ተባለ፡፡ ዕብ. 11፡6

### 3.7.2 ለድኅነት መሠረታዊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም

ለመዳን ከማመን ቀጥሎ ለድኅነት ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ቤዛነት የተገኙት የመዳን ጸጋዎች ተጠብቀው የሚገኙባቸውና እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ለሚነሡ ሰዎች የሚሰጡባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ለስም አጠራሩ ለአምላክነት ክብሩ ምስጋና ይግባውና መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን መዳን እስከ ዕለተ ምጽዓት ድረስ ለሚነሣው ለእያንዳንዱ ሰው የሚደርስለትና የሚፈጸምለት በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ነው፡፡

በምሥጢረ ጥምቀት ሥርየተ ኃጢአትን፣ ልጅነትን፣ በክርስቶስ በሞቱ መሳተፍንና ክርስቶስን መልበስን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡ በምሥጢረ ሜሮን ደግሞ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ያድርብናል፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤት እንሆናለን፡፡ በቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን የራሱን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እንበላለን እንጠጣለን፤ በዚህም የዘለዓለምን ሕይወት እናገኛለን፤ ክርስቶስን እንዋሐዳለን፡፡ በአጠቃለይ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት ምሥጢራት ዓላማቸውና አፈጻጸማቸው ሁሉ ከመዳናችን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

